ግልጽ ጥያቄ ለፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣

# የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጥብቆ ሊበቃዎት ያልቻለው እርስዎ አንሰውት ወይስ ጥብቆው በዝቶብዎት?

*(ከሔኖክ ሄደቶ፤ henhed77@yahoo.com)*

የካቲት 27 ቀን 2002 ዓ.ም ለህትመት በበቃው የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ፕ/ር በየነ ያደረጉት ቃለምልልስ ነው የፅሁፌ መነሻ ምክንያት፡፡ የህዲያ ብሄር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሀብዴድ) እና የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራሲ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) ሊቀመንበር፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት (ደቡብ ህብረት) የበላይ ጠባቂ፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) ሊቀመንበር እና የኢትዮጵያ ፌድራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የወቅቱ ሊቀመንበር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ፋኩልቲ የሥነ-ህይወት (biology) መምህር የሆኑት ፕ/ር በየነ ለጋዜጣው የሰጡት ቃለምልልስ ካለባቸው ኃላፊነት፣ ካላቸው የትምህርት ዝግጅት እና ተግባራዊ የፖለቲካ ልምድ አንፃር ብዙ ጥያቄ ሊያስነሱ የሚችሉ ሀሳቦች መሰንዘራቸው በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ቃለ ምልልሱን መነሻ በማድረግ ቢያንስ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ አስፈላጊ ነው ብዬ በማመኔ ጥያቄዎቹን ያቀረብሁ ሲሆን መልስ እንደሚያገኙ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

1) በአሁኑ ወቅት በሊቀመንበርነት የሚመሩት ‹‹መድረክ›› አባል ድርጅቶቹ ተደራድረው ያዘጋጁት መለስተኛ ፕሮግራም ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሁሉም እጩዎቹም በዚሁ መለስተኛ ፕሮግራም መሰረት ለውድድር የቀረቡ ናቸውም ብለዋል፡፡ ከስሙ እንደምንረዳው ፕሮግራማችሁ ‹‹መለስተኛ›› ሲሆን ብዙ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም አልያዛችሁም ማለት ነው፡፡ ታዲያ በመለስተኛ ፕሮግራም ሀገር መምራት ይቻላል? እንዴት? በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያልተስማሙ ፓርቲዎች የሚመሰርቱት የጥምር መንግስት ተጨማሪ ብሄራዊ እዳ ከመሆን ይልቅ አዲስ ሀገራዊ ተስፋ ለመሆን እንዴትስ ይችላል?

2) የመድረኩን ሊቀመንበርነት አመራሮቹ በየአራት ወራቱ በዙር የሚደርሳችሁ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደተመኛችሁት በምርጫው አሸንፋችሁ መንግስት የመሆን እድል ብታገኙ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱንም እንዲሁም በየአራት ወራቱ ነው የምትይዙት? መልስዎ ‹‹የለም! አንድ ሰው እንመርጣለን›› የሚል ከሆነ አሁንስ ለምን አንድ ሰው ሊቀመንበር አድርጋችሁ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲመራችሁ አትመርጡም?

3) እንደሚታወቀው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዋነኛው መገለጫ ከአስተሳሰብ ይልቅ ማንነትን መሰረት አድርጎ መደራጀት ነው፡፡ እርሶ የአብዮት ዴሞክራሲ አለመኖሩን ገልፀው እንደሚቃወሙት አስረግጠው ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል፤ የሀዲያ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ሊቀመንበር እንደመሆንዎ፣ የማንነትን መሰረት አድርጎ መደራጀትን ይደግፋሉ፡፡ ይህ ሁለቱ አስተሳሰብ እንደምን አብሮ ይሄዳል?

4) ሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መገንባት መሥራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡ አስተሳሰብን መሰረት አድርጎ በነፃነት ከመደራጀት ይልቅ በብሄር እና ብሄረሰብ መደራጀት ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት መገንባት የተሻለ ምርጫ ነው ብለው ያስባሉ? ከዚህ ጋር አያይዘው በደኢህዴን/ኢህአዴግ ውስጥ ከሚገኙ የሀዲያ ብሄር ተወላጆች እና እርሰዎ በሚመሩት ሀብዴድ ውስጥ ከሚገኙቱ የትኞቹ የበለጠ ‹‹ሀቀኛ ሀዲያ›› ናቸው ብለው ያምናሉ?

5) ‹‹ፕ/ር በየነ መቼ የህብረት ሊቀመንበር መሆን እንዳለባቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ምርጫው ሲቃረብ የመድረክ ሊቀ መንበር መሆናቸው የማይቀር ነው›› ብለው አቶ ልደቱ ፅፈው ነበር፡፡ ምርጫው ተቃርቧል፡፡ እርስዎም የመድረክ ሊቀ መንበር ሆነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የአቶ ልደቱ አባባል ከተራ ግምት ይልቅ ማንነትዎን በውል የተረዳ ትንበያ አይመስልዎትም?

6) በአሁኑ ወቅት የደቡብ ህብረት ‹‹የበላይ ጠባቂ›› እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ‹‹የበላይ ጠባቂ›› ማለት ምን ማለት ነው? በደቡብ ህብረት ውስጥ ያሉ ድርጅቶች ነፍስ እንዳላወቀ ልጅ ለምን ‹‹የበላይ ጠባቂ ሞግዚት›› አስፈለጋቸው? እንዲያው ለነገሩ፣ የበላይ ጠባቂነት አስተሳሰብ እና ድርጊት ዴሞክራሲያዊ እና ገንቢ ነው እንዴ?

7) በቅርብ ዓመታት የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) የሚባል ፓርቲ መስርተው ሊቀመንበር ሆነው መመረጥዎን ሰምተናል፡፡ ይህ ኢሶዴፓ የሚባለው ፓርቲ የፓለቲካ ፕሮግራሙ ምንድርነው? በስም የሚጠቀሱ አባላትስ አሉት? ቢያንስ አመራሩን፣ (ለምሳሌ፤ ምክትል ሊቀ በንበሩን፣ ዋና ጸሐፊውን፣ የህዝብ ግንኙነት፣...ወዘተ.) ሊያስተዋውቁን ይችላሉ?

8) የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) ሊቀመንበርም ነዎት፡፡ አሁን ደግሞ የመድረኩም ሊቀመንበር ሆነዋል፡፡ የፖለቲካውን ስራ የሚሰሩት በትርፍ ጊዜዎ ከመሆኑ አንፃር፣ በአንድ ጊዜ የአራት ድርጅቶች ሊቀመንበር ሆኖ መስራት አይከብድም? ተገቢስ ነው?

9) በአንድ ወቅት "እኔና የፖለቲካ ድርጅቶቼ" ሲሉ ሰምቼ ነበር፡፡ በአዲስ አድማስ ላኢ በሰጡት ቃለ-ምልልስዎ ደግሞ ‹‹አንድ NGO አለችኝ›› ብለዋል፡፡ ለመሆኑ ‹‹NGO መስርቼ በዋና ስራ አስኪያጅነት እመራለሁ›› ተብሎ መገለፅ ነው የሚገባው ወይስ ልክ እንደ ግል ንብረት ‹‹አለችኝ›› ተብሎ? እንዲህ ብሎ መግለፅ ከተቻለ እና ተገቢ ከሆነ ‹‹አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አለችኝ›› ብሎ መግለፅስ ለምን ስህተት ይሆናል?

10) በቅርቡ ‹‹መድሎት›› የተሰኘ መጽሐፍ የፃፉትንና በእርስዎ ላይ ትችት ያቀረቡትን አቶ ልደቱን ከዓመታት በፊት እንደሚያውቋቸው እና ‹‹ከየት ተነስተው የት እንደደረሱ›› ጠንቅቀው እንደሚያውቁ ገልፀዋል፡፡ ዋነኛ መግለጫዎም አቶ ልደቱ የመዐህድ ወጣቶች የኪነት ቡድን አስተባባሪ እንደነበሩ እና ዛሬ መጽሀፍ ለመፃፍ መብቃታቸው እንዳስገረሞት አልሸሸጉም፡፡ በርግጥ አቶ ልደቱ እድሜያቸው በሀያዎቹ መጀመሪያ በነበረበት ወቅት እርሶ ወጣቶቹን

አንቋሸው ለመግለፅ እንደሞከሩት የኪነት ቡድን አስተባባሪ ሳይሆኑ የወጣቶች ክንፍ መሪ እደነበሩ የሚታወቅ ነው፡፡ ከፍተኛ እና ውስብስብ የፖለቲካ ሂደቶችን በማለፍም ዛሬ የኢዴፓ ሊቀመንበርና በሀገሪቱ ፖለቲካ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጣሪ ሰው ለመሆን በቅተዋል፡፡ ይህ አቶ ልደቱ ያለፉበት ሂደት የሚያስተች ድክመት ወይስ አድናቆት ሊቸረው የሚገባ ጥንካሬ?

11) ስለ አቶ ልደቱ ሲናገሩ ‹‹ውርውር ሲል›› የሚል አባባል ተጠቅመዋል፡፡ በቃለ ምልልሶ መግቢያ አካባቢም አንድ ለፖለቲካ ፓርቲዎ (ለየትኛው እንደሆነ አልገለፁም) እጩ ሆኖ ስለነበረ እና ከእጩነት እራሱን ስላገለለ ሰው ሲናገሩ ‹‹የእኛ ተላላኪ የነበረ›› ብለው ገልፀውታል፡፡ እነዚህ አባባሎች ጨዋነት እና ቅንነት ያላቸው አባባሎች መስለው ይታዩዎታል? በዚሁ ቃለ ምልልስ አቶ መለስ ስለነ አቶ ስዬ ሲናገሩ ‹‹እኛ ያስወገድናቸው ርጋፊዎች ናቸው›› ማለታቸው ከእርሳቸው የማይጠበቅ መሆኑን እና የሰውን ሰብአዊ ክብር መንካት እንደማይገባ ገልጸዋል፡፡ ከእርስዎ እና ከአቶ መለስ ንግግር የትኛው የበለጠ ሰብአዊ ክብርን ይነካል?

12) አቶ መለስ ከሚተቹባቸው ነጥቦች አንዱ የስራ አስፈጻሚውን ስልጣን ጠቅልለው በብቸኝነት ለብዙ አመታት መያዛቸው ነው፡፡ የርሳቸው ተቃዋሚ የሆኑት እርስዎ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በብዛት እና ለረዥም ዘመን በመያዝ የሚታወቁ ነዎት፡፡ በዚህ ሁኔታ እርሶ አቶ መለስን ለመቃወም የሞራል የበላይነት አለኝ ይላሉ?

13) ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም ሆኑ አቶ ልደቱ አያሌው የጻፏቸውን መጽሐፍት አለማንበብዎን ገልፀዋል፡፡ በአሁኑ የሃገራችን ሁኔታ ፖለቲካው በእውቀት ሳይሆን በጭፍን ድፍንነት የሚመራ በመሆኑ የፖለቲካ መሪዎች አንባቢ እዲሆኑ የሚያስገድድ ነገር ባለመኖሩ ብዙ አልተጎዱ ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁለት የፖለቲካ መሪዎች ከእርስዎ በተስተካካይ (ቢያንስ) ተጽኖ መፍጠር የሚችሉ እና መጽሐፍቱም ሰፊ ተነባቢነት ያገኙ ከመሆኑ አንፃር አለማንበብዎ ተገቢ ነው? የአቶ ልደቱንም መጽሐፍ ‹‹መጻፍና ማንበብ ስለተቻለ ብቻ፣ አሳተምሁ ስለተባለ ብቻ መጽሐፍ መባል የለበትም፡፡ በደንብ መገምገም አለበት›› ብለዋል፡፡ ይህ ጥሩ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መጽፉን ማንበብ ‹‹ጊዜ ማባከን›› እንደሆነ አይነት ገልፀዋል፡፡ ያላነበቡትን መፅሀፍ መገምገም ይቻላል እንዴ? የመፅሀፉን ይዘት በሽፋኑ ለመገምገም መሞከርስ ለአንድ ፕሮፌሰር የሚመጥን ምክንያታዊነት ነው? መጽሐፍ አለማንበብን እንደምክር ማቅረብ የመምህርነት ሙያ ስነ-ምግባርን መጋፋት አይሆንም?

14) በ‹‹መድሎት›› ላይ ስለእርስዎ ከቀረበው ትችት አንዱ ሁለት ወጥ ማንነት ያላቸው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለመምራት መሞከርዎ ነው፡፡ ማንም ትንሽ ትንሽ ፖለቲካ ለሚገባው ሰው ህብረ ብሄራዊውን እና አስተሳሰብን መሰረት አድርጎ ተቋቋመ የተባለውን ‹‹ኢሶዴፖን›› እና የብሄር ድርጅቱን ‹‹ሃብዴድን›› በአንድ ጊዜ ለመምራት መሞከር በፖለቲካ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህን ማድረግ የቻሉ ሰው በዓለም ላይ እርስዎ ብቻ ሳይሆኑ አይቀርም፡፡ ውድ

ፕሮፌሰር፣ ማንም ያላሳካውን ይህን ድርጊት እርስዎ ምን አይነት ጥበብ ተጠቅመው ለማሳካት ቻሉ?

15) የስነ ልቦና አጥኚዎች የሰውን ልጅ ስብእና እና ባህሪ ‹‹የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የድርጊት ውጤት ነው›› ይላሉ። የእርስዎን ፖለቲካዊ ስብእና ለመገምገም ለአለፉት አስራ አምስት አመታት አስተሳሰብዎን እና ድርጊትዎን በቅርበት ከተከታተሉት ከአቶ ልደቱ የተሻለ ሰው ከወዴት ይገኛል? ከዚህ አንጻር ‹‹የእኔን ስብእና እና ውሎ ለመገምገም የርሱ ጭንቅላት አይችልም›› ብሎ ማለት ከብሽቀት የመነጨ ተራ ስድብ እና ባዶ ትምክህት ካልሆነ በስተቀር ምን ሊባል ይችላል?

16) በቃለ ምልልስዎ ‹‹የውጤት መጨረሻው ስልጣን መያዝ ነው›› ብለው ተናግረዋል። የፖለቲካ ትግል የመጨረሻ ውጤት ስልጣን ከመያዝ ባለፈ ሁለንተናዊ የህብረተሰብ እድገትን ማሳካት እንደሆነ ይስቱታል ብዬ ለማሰብ ስለምቸገር እንደ ቀላል የአነጋገር ስህተት ልውሰድልዎት። ሆኖም ስልጣን ከመያዝ በመለስ በተለያዩ ደረጃዎች ሊገለፁ የሚችሉ የፖለቲካ ድሎች እንዳሉም እንዲሁ ግልጽ ነው። ለዚህም ነው በቃለ ምልልሶ ከሽግግሩ ዘመን በኋላ ጥቂት የፓርላማ ወንበር ሃዲያ ላይ ማሸነፋችሁን እንደ አንድ ድል ቆጥረው የተኩራሩት። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የተለያዩ ህብረቶችን መርተው ለተሻለ ፖለቲካዊ ድል ማብቃት ባለመቻልዎ የሚቀርብብዎትን ትችት በቅንነት ተቀብለው ለማስተካከል የማይሞክሩት ለምንድርን ነው? ይህን ትችት ከሚያቀርቡት ሰዎች መካከል አቶ ልደቱ እና ዶ/ር ብርሃኑ ይገኙበታል። እነዚህ ፖለቲከኞች በ1997ቱ ምርጫ አመራር ሆነው በተሳተፉበት ቅንጅት መፍጠር የቻሉት ህዝባዊ ንቅናቄ እና የለውጥ ትኩሳት እርስዎ ለሚመሩት ህብረትም ተርፎ በራስዎ ሰርተው ካሳኩት ውጤት በአራት እጥፍ የበለጠ እንዲያገኙ እንዳስቻለዎት እውቅና መስጠት ለምን ከባድ ይሆንብዎታል?

ውድ ፕሮፌሰር በየነ፣ እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረብኩልዎ ለጥያቄዎቹ መልስ እንደሚያቀርቡ ተስፋ በማድረግ ሲሆን፤ ጥያቄዎቼንም ለማቅረብ ያነሳሳኝ አንዱ ምክንያት ለእርስዎ ለራስዎ ከማሰብ ነው። ከቃለ ምልልስዎ የተገነዘብሁት አንድ ነገር ተክለ-ሰውነትዎ ለፖለቲካው ጥብቆ የማነስ ከፍተኛ አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን ሲሆን፣ ጥያቄዎቹም የቀረቡት እነርሱን ለመመለስ በሚደረግ ጥረት ተክለ-ሰውነትዎ ጥብቆውን እስኪሞላ ድረስ የመፈርጠም ተስፋ አለው ብዬ በማመኔ ነው- ጥብቆው መጠኑ እየጨመረ እንጂ እያነሰ የመሄድ ተፈጥሯዊ ባህሪ የለውምና። ይህን ማድረግ ከቻሉ በርዕሱ ላይ ያቀረብሁት ጥያቄ በአውንታዊነት ተመለሰ ለማለት ይቻላል።